# ኢትዮጵያዊነት መንፈስ ነዉ።

*የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተክርስትያን፣ኢትዮጵያ እና ኢትዮጵያዊነት ቢሸሹት የማይሸሽ መፈስ ሆኖባቸው መነሻውን ለማጥፋት የሚዳክሩ የኢትዮጵያ ጠላቶች ሰዎችና ማኒፌስቶ ይገርሙኛል። ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ኢትዮጵያ እና ኢትዮጵያዊነት እኮ የነቢያትን ትንቢት ተቀብለው የጌታን መወለድ ጠብቀው የኖሩ እና በልደቱም ተገኝተው ገጸበረከት ያቀረቡ ናቸው።።ኢትዮጵያ እና ኢትዮጵያዊነት አያረጅም ኢትዮጵያ እና ኢትዮጵያዊነት ቢሸሹት የማይሸሽ አለም ከዚህ የአሸናፊዎች አሸናፊ መፈስ አረንጓዴ ቢጫ ቀይ የነፃነት ሰንደቅ ምንጭ ጠጥቶ ረክቶአል።* **ኢትዮጵያዊነት መንፈስ ነዉ።**



*በአገር ቤትና ከአገር ዉጭ ያለን፣ እዉነትን ለኢትዮጵያ የተጠማን ኢትዮጵያዊያን ሁሉ መንፈሰ ቆራጥ መሆን ይጠበቅብናል::የእዉነት ለዉጥ በወሬ አይመጣም፣ ለዉጥ መግለጫ በማውጣት ጋጋታ ብቻ አይመጣም፣ ወይንም በቴሌቭዥን አይመጣም፣ ለዉጥ በምኞት ትችት አይመጣም። የኢትዮጵያ ለውጥ የሚመጣው በትግል፣ በስራ፣ በትብብር፣ በቁርጠኝነትና እያንዳንዱ ዜጋ የድርሻውዉን በማበርከት ነው። ለውጥ የሚመጣዉ በሙሾ ነጋሪነት ሳይሆን በዛሬ ቁርጠኛ ትግል ነው።ለዚህ ደግሞ ሁሉም መንፈሱ ኢትዮጵያዊ የሆነ ሁሉ ያስፈልገናል።*

**ኢትዮጵያዊነት መንፈስ ነዉ ።** *ገብርኤል ብዙነህ 09/19/2020 ሰሜን አሜሪካ*